# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ፊልሞና

1 የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ ከሆነው
ከጳውሎስና ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ፤

ለውድ ወዳጃችንና አብሮን ለሚሠራው
ለፊልሞና፣ 2ለእኅታችን ለአፍብያ፣ አብሮን
ወታደር ለሆነው ለአርክጳ በቤትህም ላለ
ችው ቤተ ክርስቲያን፤

3ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

4አንተን በጸሎቴ በማስብህ ጊዜ ዘወትር
አምላኬን አመሰግናለሁ፤ 5ምክንያቱም በጌታ
በኢየሱስ ያለህን እምነትና ለቅዱሳንም
ሁሉ ያለህን ፍቅር ሰምቻለሁ። 6በክርስቶስ
ስላለን መልካም ነገር ሁሉ በሚገባ ትረዳ
ዘንድ፣ እምነትህን ለሌሎች በማካፈል
እንድትተጋ እጸልያለሁ። 7ወንድሜ ሆይ፤
የቅዱሳንን ልብ ስላሳረፍህ ከፍቅርህ ታላቅ
ደስታና መጽናናት አግኝቻለሁ።

8ስለዚህ ማድረግ የሚገባህን እንድታደርግ
አዝህ ዘንድ በክርስቶስ ድፍረት ቢኖረ
ኝም 9በፍቅር እለምንሃለሁ፤ እንግዲህ ሽማ
ግሌና አሁን ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስ
እስረኛ የሆንሁት እኔ ጳውሎስ፣ 10በእስር
እያለሁ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲ
ሞስ[ሀ] እለምንሃለሁ። 11አስቀድሞ የሚጠ
ቅምህ አልነበረም፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ
ለእኔ የሚጠቅም ሰው ሆኖአል።

12የልቤ ሰው የሆነውን እርሱን መልሼ
ወደ አንተ ልኬዋለሁ። 13ስለ ወንጌል
በታሰር ሁበት ጊዜ በአንተ ፈንታ ሆኖ
እንዲያገለግለኝ ለራሴ ላስቀረው ፈልጌ
ነበር፤

14ነገር ግን አንተ የምታደርገውን መልካም
ነገር ሁሉ በውዴታ እንጂ በግዴታ
እንዳ ይሆን ሳላማክርህ ምንም ማድረግ
አል ፈልግም። 15ምናልባት ለጥቂት ጊዜ
ከአንተ የተለየው፣ ተቀብለህ ለዘለቄታው
አንተ ዘንድ እንድታቈየው ነው፤ 16ከእን
ግዲህ ወዲህ ግን እንደ ባሪያ ሳይሆን
ከባሪያ በላይ የሆነ ተወዳጅ ወንድም ነው።
ለእኔ ተወዳጅ ነው፤ ለአንተ ግን በሥጋም
በጌታም ይበልጥ ተወዳጅ ነው!።

17እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ከቈጠርኸኝ
እኔን እንደምትቀበለኝ አድርገህ ተቀበለው።
18አንተን የበደለህ ነገር ቢኖር ወይም የአንተ
ብድር ቢኖርበት በእኔ ላይ ቍጠረው። 19እኔ
ጳውሎስ ይህን በእጄ ጽፌልሃለሁ፤ ያለ
በትን እኔው እከፍልሃለሁ። አንተም ራስህ
የእኔ ስለ መሆንህ ምንም አልናገርም።
20ወን ድሜ ሆይ፤ በጌታ እንድትጠቅመኝ
እፈል ጋለሁ፤ በክርስቶስ ልቤን
አሳርፍልኝ። 21ታዛዥ መሆንህን በመተ
ማመን፣ ከምጠይቀውም በላይ
እንደምታደርግ በማወቅ እጽፍልሃለሁ።

22ከዚህም ሌላ፣ ጸሎታችሁ መልስ አግኝቶ
ወደ እናንተ ለመምጣት ተስፋ ስለማደርግ
ማረፊያ አዘጋጅልኝ።

23ከእኔ ጋር የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ
የሆነውኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብልሃል፤

24እንዲሁም አብረውኝ የሚሠሩት ማር
ቆስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ዴማስና ሉቃስ ሰላምታ
ያቀርቡልሃል።

25የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመን
ፈሳችሁ ጋር ይሁን።

[ሀ]10 አናሲሞስ ማለት የሚጠቅም ማለት ነው

1፥1 ቆ 9፡23፤ ሐሥ 16፥1፤ 2ቆሮ1፥1፤ኤፌ3፥1፤ ፊል2፥25
1፥2 ሮሜ16፥5፤ ፊል2፥25፤ቈላ4፥17
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ሮሜ1፥8፡10
1፥5 ሐሥ20፥21፤ ቈላ1፥4፤1ተሰ3፥6
1፥7 ቆ 20፤ ሮሜ15፥32፤ 1ቆሮ16፥18፤ 2ቆሮ7፥4፥13
1፥9 ቆ 1፡23፤ 1ቆሮ 1፥10፤ኤፌ3፥1
1፥10 ሐሥ21፥33፤ ቈላ4፥9፤1ተሰ2፥11
1፥13 ቆ 10፤ ሐሥ 21፥33
1፥14 2ቆሮ9፥7፤ 1ጴጥ5፥2
1፥16 ማቴ23፥8፤ ሐሥ1፥16፤ 1ቆሮ 7፥22፤ 1ጢሞ6፥2
1፥17 2ቆሮ8፥23
1፥18 ዘፍ43፥9
1፥19 1ቆሮ16፥21
1፥20 ቆ 7፤ 1ቆሮ 16፥18
1፥21 2ቆሮ2፥3
1፥22 2ቆሮ1፥11፤ ፊል1፥19፡25፤2፥24፤ ዕብ13፥19
1፥23 ቆ 1፤ሮሜ 16፥7፤ቈላ1፥7፤4፥10
1፥24 ቆ 1፤ሐሥ 12፥12፤19፥29፤ ቈላ 4፥14፤ 2ጢሞ4፥10
1፥25 ገላ6፥18